የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 40
ADDIS ABABA 3rd June, 1997

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፸፯/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ (ማሻሻያ) አዋጅ ........ ገጽ ፭፻፳፬

CONTENTS

Proclamation No. 77/1997
Sales and Excise Tax (Amendment)
Proclamation ........................................ Page 524

## አዋጅ ቁጥር ፸፯/፲፱፻፹፱

### የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ ፤ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፸፯/፲፱፻፹፱» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፷፰/፲፱፻፹፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል ፤

፩· የአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፫)(ሀ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫)(ሀ) ተተክቷል ፤
«፫(ሀ) ግብር ከፋዩ አምራች ፣ አገልግሎት ሰጪ ፣ ጅምላ ሻጭ ወይም ቸርቻሪ ሲሆን ፣ በአንድ ወር ውስጥ በተከናወነው ሽያጭ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ ወሩ ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ እጅግ ቢዘገይ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ የማሳወቅና ታክሱን የመክፈል ግዴታ አለበት ።»

## PROCLAMATION NO. 77/1997

### A PROCLAMATION TO AMEND THE SALES AND EXCISE TAX PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Sales and Excise Tax Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
   This Proclamation may be cited as the "Sales and Excise Tax (Amendment) Proclamation No. 77/1997."
2. *Amendment*
   The Sales and Excise Tax Proclamation No. 68/1993 is amended as follows:
   1) Sub-Article (3) (a) of Article 8 is deleted and replaced by the following new sub-Article (3) (a):
      "3(a) Where the tax payer is a producer, service supplier, wholesaler or retailer, he shall declare and pay the tax on a monthly sales transaction within seven working days from the end of the month, at the latest."

፪. ከአዋጁ ጋር የተያያዘው ሠንጠረዥ «መ» ተራ ቁጥር ፩፣ ፪.፪ ፣ ፪.፫.፫ ፣ ፫ ፣ ፭.፪ ፣ ፮ እና ፲፯ ተሠርዘው በሚከተሉት ተራ ቁጥሮች ተተክተዋል ፤

"፩. ማናቸውም ዓይነት ስኳር (ሞላሰስን ሳይጨምር) ....................................... ፴፫%
"፪.፪ የሚኒራል ውሃ .................... ፵%
"፪.፫.፫ ሌሎች አልኮል ያለባቸው መጠጦች ............... ፶%
"፫. ማናቸውም ዓይነት ንጹህ አልኮል .............. ፻፶%
"፭.፪ ሲጋሬት ፣ ሲጋራ ፤ ሲጋራሎስ ፣ የፒፓ ትምባሆ ሱረትና ሌሎችም የትምባሆ ውጤቶች ..................................... ፸፭%
"፮. ጨው .................................................. ፴%
"፲፯. ላንድሮቨሮች ፣ ጂፖችና ሌሎች እነዚህን መሰል ፎርዌል ድራይቮች ........................ ፵%

፫. ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ (፬) የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ከአዋጁ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ «መ» ተራ ቁጥር ፪.፩ እና ፪.፫.፩ የተመለከቱት የማስከፈያ ልኮች በሚከተለው እንዲተኩ እንዲያደርግ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

"፪.፩ ማናቸውም ለስላሣ መጠጦች (ከፍሬ ጭማቂዎችና እነዚህን ከመሳሰሉ በስተቀር) .......... ፵%
"፪.፫.፩ ማናቸውም ቢራና እስታውት .......... ፶%

፬. ቅድመ ሁኔታዎች

ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው ተፈጻሚ የሚሆነው ፤

፩. ለስላሳ መጠጦችን በሚመለከት ፣ የለስላሳ መጠጦች ምርት በ፸ % (በሰባ በመቶ) ሲያድግ ወይም አዳዲስ የለስላሳ መጠጦች ፋብሪካዎች ሲቋቋሙ ፤
፪. ቢራን በሚመለከት ፣ የቢራ ምርት በ፶ % (በሃምሣ በመቶ) ሲያድግ ወይም አዳዲስ የቢራ ፋብሪካዎች ሲቋቋሙ ፤

ይሆናል ።

፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ፣ ግንቦት ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2) Numbers 1, 2.2, 2.3.3, 3, 5.2, 6 and 17 of Schedule D attached to the Proclamation are deleted and replaced by the following numbers:

"1. Any type of sugar excluding molasses 33%
"2.2 Mineral Water .................................. 40%
"2.3.3 Other alcoholic drinks ...................... 50%
" 3. All types of pure alcohol ................. 150%
"5.2 Cigarettes, cigar, cigarillos, pipe tobacco, snuff and other tobacco products .............................................. 75%
" 6. Salt.................................................. 30%
"17. Land Rovers, Jeeps and other Fourwheel Drives ............................. 40%

3) The Minister of Finance is hereby empowered to substitute the rates indicated below for their counterparts in numbers 2.1 and 2.3.1 of Schedule D attached to the Proclamation, if satisfied that conditions listed under sub-Article (4) hereunder are fulfilled:

2.1 All types of soft drinks except squash and similar juices ....................................... 40%
2.3.1 All types of beer and stout ................. 50%

4) Conditions Precedent

The provisions of Sub-Article (3) above become applicable:

1. In the case of soft drinks, where the production has increased by 70% (seventy percent) or new factories thereof are established.
2. In the case of Beer, where the production has increased by 50% (fifty percent) or new breweries are established.

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 3rd day of June, 1997.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of June, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE